# የነጭ ለባሾቹ ተደጋጋሚ "መዝሙር"

**ሰላም መላኩ** 12-26-14

ባህር ማዶ ቁጭ ብለው ስለ ሀገራችን መጥፎ ነገሮችን በስሚ ስሚ እየለቃቀሙ ያላወሩበትንና ያላሟረቱበትን ቀን አላስታውስም ፡፡ ዛሬ ለእነርሱ ትናንት እንጂ ዘንድሮ አይደለም፡፡ የዛሬ መነፅራቸው በትናንት እነርሱነታቸው ላይ የተሰካ ከመሆኑም ባሻገር፤ በጋዜጠኝነት ስም የተሰማሩበት "የነጭ ለባሽነት" ፖለቲካዊ ተልዕኮ ዕውነታውን እንዳይመለከቱ የጋረዳቸው ናቸው።

በዚህም ሳቢያ ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይተዋወቁ፣ ሽብርንና ሽብርተኝነትን የሚያንቆለጳጵሱ እንዲሁም በፈጠራ ጭምር ታግዘው የሚያቀርቧቸውን የአንድ ወገን ዘገባ ፅንፈኛ አጀንዳዎችን እየገረመንም ቢሆን ማድመጥ ከጀመርን ዓመታትን አስቆጥረናል –እኔን መሳይ እፍኝ የማንሞላ አድማጮቻቸው፡፡

በሀገራችን ዕድገት ሁሌም ዓይኑ ደም ከሚለብሰው የኤርትራ መንግስት የውሸት ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የሆኑት ቴሌቪዥንና ሬዲዮ አምሳያ ናቸው።…እናንተዬ ማን ነበር "አምሳያዬ ነሽ…"ያለው?– አዎ! እነርሱ እንዲያ ናቸው።…እናም ኢትዮጵያን በተመለከተ የሚያቀርቧቸው አጀንዳዎች፣ የሚዲያው ባለቤት ስም የሚለያቸው ካልሆነ በስተቀር ከሻዕቢያው "አፈ-ቀላጤዎች" ጋር ምንም ዓይነት ባህሪያዊ ልዩነት የላቸውም።

ልክ እንደ ሻዕቢያው የፕሮፖጋንዳ ማሽኖች ሁሉ፤ ከጋዜጠኝነት ስነ–ምግባር ውጭ የሆኑ፣ሚዛናዊነት የጎደላቸውና በፍፁም ጥላቻ ላይ ተመስርተው የሚያቀርቧቸው ሀገርን የሚያጥላሉ፣ ከመንግስታቸው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ውጪ ሽብርተኝነትን የሚያበረታቱና የልማት ጥረትን የሚያሰናክሉ የዘገባቸው ዓይነቶች ህልቆ መሳፍርት የላቸውም፡፡

መቼም ውድ አንባቢዎቼ ስለእነማን እያወጋሁ እንደሆነ የምትገነዘቡ ይመስለኛል። እርግጥም የወጌ ማጠንጠኛ በቅብብሎሽ ድራማዊ ጨዋታ የሀገራችንን ገፅታ ለማጠልሸት የሚሯሯጡት "እነ ቪኦኤ" እና የጀርመን ድምፅ ሬድዩኖችን ነው–በተለይም የአማርኛ

ክፍሎቻቸውን፡፡ ታዲያ ምናልባት ዘገባቸውን የሚያዳምጥ ሰው ካለ ሊደመም አይገባም፡፡ ሆኖም አንድ ዕውነታን መጠርጥር ግን የግድ ይለዋል–ተግባሩ ከበስተጀርባው ርዕዮተ-ዓለማዊ ተልዕኮን አንግቦ የሚከናወን መሆኑን፡፡ ለነገሩ ለእነዚህ ሚዲያዎቸ እውነት ማለት ኢትዮጵያን የሚቃረንና የፅንፈኛ ፖለቲከኞች መግለጫ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም በየምሽቱ እንግዳችን፣ምሁራችን፣ተንታኛችን…ወዘተ እያሉ በማንቆለጳጰስ የሚያቀርቧቸው የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል መሪዎችና የመግለጫ ጋጋታቸው፣ውጭ የሚኖሩ የቀድሞ ስርዓት ናፋቂዎችና ሀገራችን በወንጀል የምትፈልጋቸው ግለሰቦቸ አስረጅ አብነቶች ናቸው፡፡

ምንም እንኳን ሚዲያዎቹ በመዲናችን ውስጥ አድማጮቻቸው ተደምረው ሁለት በመቶ የማይሆኑ መሆኑን በቅርቡ የወጡ ጥናቶች ቢያመለክቱም፤ሀገራችን ከራሷ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የነደፈችውን የልማት ስትራቴጂ እንዳታሳካ እንቅፋት በመሆን የፅንፈኛ ኒዮ- ሊበራል ተላላኪነታቸውን ገቢራዊ ለማድረግ የስርጭት ሰዓታቸውን እስከመቀየር የደረሱ ናቸው፡፡ እኔም እንደ ዜጋ የእነዚህን "ሞትኩ ለሆዴ" ኢትዩጵያዊ ያልሆኑ ኢትዩጵያዊያንን ፀረ-ሀገር ሴራ ለአንባቢዎቼ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ እንዲህ አቅርቤዋለሁ፡፡

ትናንት የአረቡ ዓለምና የሰሜን አፍሪካው ህዝባዊ ተቃውሞ በሌለ ነባራዊ ሁኔታው ወደ ኢትዮጵያም እንዲመጣ 'ሱባኤ' ሲገቡ፣ በየትኛውም የዓለም ክፍል የተከሰተው የኑሮ ውድነትን ሀገራችን ውስጥ ብቻ እንደተፈጠረ አስመስለው ሲደሰኩሩ፣ የዓባይ ግንባታ አይሳካም እያሉ አሟርተዋል–በተመሳሳይ "መዝሙር"።

የመምህራኑን ፍትሐዊ ጥያቄ በራሳቸው ጠመዝማዛ እሳቤ ገልብጠው በማቅረብ ሲያቀጣጥሉ፣ ሀገራችን ያልለማና ጠፍ መሬቷን ለማልማት ደፋ ቀና ስትል የአክራሪ ኒዩ-ሊበራሊዝም ሃይሎች አፈ-ቀላጤ በመሆን 'የመሬት ወረራ ተካሄደ' የሚል አፈ-ታሪክን ሲቀምሩ ከርመዋል። ዛሬ ደግሞ እንደምንም ተንገታግተው የሃይማኖት ፖለቲካን የማራገብ ተግባራቸውም ላይ ደርሰዋል፤ ያለ አንዳች ውጤት ባዶ እጃቸውን እያጨበጨቡ።

የሙስሊሙን ሃይማኖት የማይወክሉ ጥቂት አክራሪዎችን በመደገፍም ከአወሊያው ፖለቲካዊ ትዕይንት እስከ "የሙስሊሙ ተወካይ ነን" የሚሉ የሁለት ሰው ጣቶችን እንኳን የማይሞሉ የሽብርተኝነት ተጠርጣሪ ግለሰቦች ድረስ በአይዞህ ባይነትም ተሰልፈዋል–

ሲያሻቸው በፍርድ ቤት የተያዘ ጉዳይን ሙሉ ብይን በመስጠት፣ በል ሲላቸው ደግሞ ተጠርጣሪዎቹን ከተከሰሱበት ጉዳይ ጋር ምንም ዓይነት ንክኪ የላቸውም እያሉ በመወሰን።

አጀንዳቸው ኢትዮጵያ ውሰጥ አለመረጋጋት ተፈጥሮ ማየት በመሆኑም፤ ከመሰንበቻው ደግሞ የዚሁ ፍላጎታቸው ተቀጥያ የሆነውንና በየመስጊዱ የሚሰባሰቡ ጥቂት ግለሰቦችን በመጥቀስ ሃይማኖታዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ ዓላማቸው ከግቡ ይደርስ ዘንድ ያለመታከት እየሰሩላቸው ነው፤ እነ ቪ.ኦ.ኤ።

ይህ ብቻም አይደለም። በአንዳንድ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የተከሰተንና ጉዳዩ እየተጣራ የሚገኝን ጊዜያዊ ችግር በማራገብ የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎችን የቀለም አብዩት ናፋቂነት ወኪል ሆነውም ሰርተዋል፤ እየሰሩም ነው። በዚህም ማንነታቸው በውል የማይታወቁ የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ሙስሊም ተማሪዎችን ስም በመጥቀስ በየምሽቱ "አንዲት ተማሪ እንዲህ አለች..." እያሉ በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን የቅብብሎሽ አጀንዳቸው ሰለባ ለማድረግ ባተሌ ሆነውም ሰንብተዋል። ምንም እንኳን ይህ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ዜጎችን የማበጣበጥ ህልማቸው ዛሬም እንደ ትናንቱ የሚሳካላቸው ባይሆንም።

ታዲያ እዚህ ላይ አስገራሚው ነገር የአሜሪካው ድምፅ በተለይም የአማርኛው ክፍል ያቋቋመውን መንግስት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተፃርሮ እየሰራ መሆኑ ነው። እንደሚታወቀው የአሜሪካ መንግስት በሽብርተኝነትና በአሸባሪዎች ላይ የማያወላዳ አቋም እንዳለው ከማናችንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም።

በተለይም ከመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት በኋላ በማንኛውም ጊዜና ወቅት ሽብርተኝነትን ከሚያወግዙ ሀገራት ጋር እጅና ጓንት በመሆን ይህን አስከፊ ተግባር ከዓለማችን ለማሰወገድ በቁርጠኝነት በመስራት ላይ ይገኛል።

ይሁንና የአሜሪካው ድምፅ የአማርኛው ክፍል ይህን የሀገሩን ፖሊሲ እንዳላየ በማለፍ በሽብር የሚጠረጠሩ ሃይሎችን እያበረታታ ነው። አሜሪካ ውስጥ የሚጠረጠሩ የአል-ቃዒዳ ስኬቶች (ምናልባት ካሉ ማለቴ ነው) የማይዘገቡት ከሀገሪቱ ፖሊሲ በመነሳት መሆኑን እያወቀ፤ በኢትዮጵያ የአየር ሞገድ ውስጥ ተጠርጣሪ አሸባሪዎችን ማበረታታት

እንዲያውም እንደ ፍርድ ቤት ብይን እስከ መስጠት ደርሶ "ነፃ" መሆናቸውንም የሚያውጅበት አመክንዮ ለማንም ሰው ግልፅ አይደለም።

ታዲያ ይህ የራስን መንግስት ፖሊሲ ተፃርሮ ቆሞ የሌሎች ሀገራትን ሰላም በአሉባልታ ወሬ ለማወክ የመሞከር ጥብቅ ፍላጎት ጋዜጠኞቹ ከጀርባቸው ይዘውት የሚዘውሩት አንዳች ርዕዩተ-ዓለማዊ አጀንዳ እንዳለ ለመገመት ብዙም ምርምር የሚጠይቅ አይመስለኝም።

እናም ሃቁን ለመገንዘብ የዋሽንግተኑ ጋዜጠኞች አሰራርን እንዲሁም የሚሰሩበትን እውነተኛ ርዕዩተ-ዓለማዊ ምህዳርን መዳሰስ ተገቢ ይመስለኛል። የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው በየትኛውም ሀገር የሚከናወን የጋዜጠኝነት አሰራር ሙያዊ ስነ-ምግባር ውስጥ ቃለ-መጠይቅ ተደራጊው ግለሰብ ለየትኛውም ወገን የማይወግን መሆን ይኖርበታል፡፡

ከዚህ ውጪ አንድን ግለሰብ ብቻ በመጠየቅ የሚከናወን መጠይቅ በቀጥታ ከጋዜጠኛው የፖለቲካ ወገንተኝነትና ፍላጎት ጋር የሚያያዝ ይሆናል፡፡ የቪኦኤ ጋዜጠኞች ግን የሚያከናውኑት ተግባር የማይወግኑ ግለሰቦችን በማቅረበ ሳይሆን፤ የተቃውሞ ተጋሪያቸው የሆኑ ሰዎችን ካሉበት ቦታ አነፍንፈው በማስመጣት አሊያም ስልክ ደውለው ፀረ-ኢትዩጵያ አቋማቸውን እንዲያራግፉ በማድረግ ኢ-ሙያዊ ተግባርን በመፈፀም ነው፡፡

በዚህም የተዛባ ሚዛን ያለውን ዘገባ ለአድማጮቻቸው በማቅረብ ሙያዊ ስነ-ምግባራቸውን ይጥሳሉ–ከቶ እነርሱ ማን ከልካይ አላቸውና?...ምናልባትም ጋዜጠኞቹ ቅምሻ ዓይነት ዘገባዎችን በማጣቀስ "የመንግስት ደጋፊዎችንም ሃሳብ አናካትታለን" ሊሉ ይችሉ፡፡ ዕውነታው ግን በፍፁም ይህ አይደለም።…

የአንድ ሬድዮ ጣቢያ ሚዛናዊነትና ርቱዕነት የሚገለፀው ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች ላሏቸው ወገኖች እኩል ዕድል በመስጠቱና ባለመስጠቱ ነው፡፡ በዚሀ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት፤ቪ.ኦ.ኤ የሚያስተላልፉቸው ዘገባዎች እጅግ በርካታ የሆኑት (ምናልባትም ከ90 በመቶ በላይ) የጋዜጠኛው ፖለቲካዊ ዝማሜ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ዘገባዎች ደግሞ አጠቃላይ ዕውቀትንና እዚህ ግባ የማይባሉ የኢትዮጵያ

መንግስት ተግባራት ተጣመው የሚቀርቡበት ማደናገሪያዎች ከመሆን የሚዘሉ አይደሉም።

እንግዲህ ልብ በሉ! “ስለ ጋዜጠኝነት መከበር” ሲ.ፒ.ጄን የመሳሰሉ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል እየጠቀሱ የሚደሰኩሩት የቪ.ኦ.ኤ ጋዜጠኞች፣ራሳቸው በዚህ ሁኔታ የሙያውን ስነ-ምግባር የሚደፈጥጡ ናቸው።…እናንተዬ ነገሩን “ሰይጣን ላመሉ ከመፅሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል” እንዲሉት ዓይነት ነው እንበለው እንዴ?…

ታዲያ የራሳቸው የፖለቲካ አመለካከት የታጨቁባቸውን የአንድ ወገን የጥላቻ ዘገባዎችን የሚያሰራጩትን እነዚህን ኃይሎች፣ ሲ.ፒ.ጄ ተብዬው ድርጅት በጋዜጠኝነት የሚያወቃቸው አይመስልም። ምክንያቱ ሌላ እንዳይመስላችሁ—የእነ ቪ.ኦ.ኤ ጋዜጠኞች በገሃድ ከሚያከናውኑት የጋዜጠኝነት ሽፋናቸው በተጨማሪ፣ ሲ.ፒ.ጄንና ሂዩማን ራይትስ ዎችን ለመሳሰሉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች የስለላ ስራም ስለሚያከናውኑ ነው።

አንድ ለሚዲያዎቹ ቅርበት ያለው ወዳጄ እንዳወጋኝ ከሆነ ፣እነ ቪ.ኦኤ የፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች ሰላይ ናቸው። ግና እንዴት? ብላችሁ መጠየቃችሁ አይቀርም—ነገሩ ግን ወዲህ ነው።…

…ገና ከጅምሩ እነ ቪ.ኦ.ኤ የተደራጁት በጋዜጠኝነት ስም ከእነዚህ ኃይሎች ጋር “ዞሮ-ገጠም” ክብ እንዲሰሩ ተደርገው ነው። ጉዳዩን በአጭሩ ለመግለፅ ያህል፤ እነ ቪ.ኦ.ኤ ለጋዜጠኝነት ዘገባ በሚል አካባቢያዊ ሪፖርተሮችን በየሀገሩ ይመድባሉ ወይም ይቀጥራሉ።

ለዘጋቢዎቹም በሀገራቱ ውስጥ ከነባራዊው ሁኔታ ውጪ የሆኑ ፍፁማዊ (absolute) የሰብዓዊ መብት፣ የፕሬስ ነፃነት፣ የዴሞክራሲ ጉዳዮች…ወዘተ. አለመከናወናቸውን የሚያትቱ ዘገባዎችን ነቅሰው እንዲልኩ ጥብቅ ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ። ሪፖርተሮቹም ይህንኑ ያደርጋሉ።…

…እነ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ሲ.ፒ.ጄና አምንስቲ ኢንተርናሽናልን የመሳሰሉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎችም፤ በየሀገሩ ከፈለፈሏቸው ተቃዋሚዎችና “ጉዳይ ፈፃሚ” የፕሬስ ውጤቶች

ከሚደርሷቸው ስብቀቶች በተጨማሪ፤ የቪ.ኦ.ኤን ዘገባም በሪፖርትነት እንዲቀርቡላቸው ይደረጋል፤ መዝግበውም ይይዟቸዋል።

ከዚያም ከእነርሱ አመለካከት ውጪ በራሳቸው የልማት አማራጭ ማደግ በጀመሩ እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት ሀገራት ላይ በየሁለት ወሩ ሪፖርቱን ተመርኩዘው የመግለጫ ጋጋታ ያወጣሉ። መግለጫውን ደግሞ ተላላኪዎቹ የቪ.ኦ.ኤ. ጋዜጠኞች ቅድሚያውን ወስደው ያንበለብሉታል።

በዚህም የመግለጫው የመጀመሪያና የመጨረሻ ተወናዮች ዋሽንግተን የሚገኙት ጋዜጠኞች ይሆናሉ ማለት ነው። እናስ በጋዜጠኝነት ስም የስለላ ተግባር "አልፋና ኦሜጋ" መሆን እንዲህ አይደለምን?– መረጃ ካቀረቡ በኋላ መልሶ የራስን መረጃ የማነብነብ ድንቅ ተልዕኮ። ታዲያ እንዲህ ዓይነቱን "ወደር የለሽ ተላላኪ" ማነው ለጋዜጠኝነት ስነ-ምግባር ብሎ የሚነካው?– እነ ሲ.ፒ.ጄ እጃቸውን በእጃቸው የመቁረጥ አባዜ ከሌለባቸው በስተቀር፡፡

እዚህ ላይ ውድ አንባቢዎቼ እንዲገነዘቡልኝ የምፈለገው ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም በዚህ ሁኔታ የተላላኪነት ስራቸውን የሚያከናውኑት የጣቢያው ጋዜጠኞች፤ በዋነኛ አዳማቂነት "ስልክ እየደወላችሁ የኢትዮጵያን መንግስት አውግዙ" የሚሏቸውን እንዲሁም "ምሁር እገሌ" እያሉ የሚያቀርቧቸውንና ሌሎች ፀረ-ሀገርና ፀረ-ህዝብ ሃይሎችን የሚጠቀሙ መሆናቸውን ነው፡፡

በኦነጋዊ አስተሳሰባቸው የሚታወቁትን እነ ሲራጅ መሐመድን፣ በሀገራችን ህዝቦች በወንጀለኝነታቸው በጥብቅ የሚፈለጉት እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋንና ጭፍራዎቻቸውን ብሎም ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ያለ አቅሙ እንቶ ፈንቶ ወሬ በመቀበጣጠር የሚታወቀውን ታማኝ በየነን /በደርግ ወቅት የስርዓቱ ታማኝ ኮሚዲያን የነበረና አሁን ደግሞ ወደ ፖለቲካ ሙሾ አውራጅነት የተቀየረ/ እንዲሁም ትንቢት ተናጋሪው ስዬ አብርሃንና የነውጥ አጋሮቻቸውን ለበርካታ ወራት የአመፅ ተንታኞችና ስትራቴጂ አውጪዎች አድርጐ ቪኦኤ በተለያዩ ጊዜያት ቢያቀርብም ሰሚ ጆሮ አላገኘም።

ዛሬ ደግሞ "ማርሹን" ቀይሮ ከድህነት ለመውጣት የሚታትር ህዝብን ሞራል ለመንካት አየቧቸረ ነው– ከሚያስተዳድረው መንግስት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዕውቅና ውጪ ሽብርተኝነትን በመደገፍ፡፡

ምንም እንኳን ጣቢያው እንዳለፉት ጊዜያት ልማትን በማደናቀፍ ሀገርን ለመበታተን የሚያደርገው ጥረቱ ዛሬም የሚሰምርለት ባይሆንም፤ በጋዜጠኞቹና እፍኝ በማይሞሉ ወዳጆቹ የሚቀርቡ ጥላቻን ያረገዙ ዘገባዎቹ ሀገራችን እንዳታድግና ሁሌም ተመፅዋች ሆና እንድትቀር ያላቸውን ፍላጐት ፍንትው አድርጐ የሚያሣይ ነው፡፡

ይሁንና የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደ እኔ የዋህ አሳቢ ሆኖ 'የዋሽንግተኖቹ ጋዜጠኞች ኢትዮጵያውያን ሆነው ሳለ፣ ለምን ይህን መሰሉን አክራሪነትን የማበረታታት ሴራ ይፈፅማሉ?' ብሎ ራሱን ሊጠይቅ ይችላል። አዎ! ምንም እንኳን ጥያቄው ተገቢ ቢሆንም፤ የእውነታው ጓዳ ተገልጦ ሲታይ ግን ይህን የሚመስል ነው።…

…ዋሽንግተን የሚገኙት የቪ.ኦ.ኤ. ጋዜጠኞች የቀድሞው ስርዓት አቀንቃኞች፣ የኢህአፓ ርዝራዦች ከመሆናቸውም በላይ፤ ከኢትዮጵያ ፀረ-ሰላም ሃይሎችና አሸባሪዎች ጋር የጠነከረ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን በቅርበት የሚያውቋቸው ወገኖች ይናገራሉ።

የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ ገሸሽ አድርገው በኢትዮጵያ ላይ የሚነዙት አሉባልታም ምናልባት በአንድ በኩል ሲታይ ቀደምት ሽንፈታቸውን ለማካካስ አሊያም "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" በሚል ብሂል የሀገራችን ፀር ለሆኑ ሃይሎች እየሰሩ ሊሆን እንደሚችል እነዚሁ ወገኖች ያረጋግጣሉ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ጋዜጠኞቹ ምንም ዓይነት ሚዛናዊ እሳቤ የሌላቸው መሆናቸውን ተግባራቸው አፍ አውጥቶ ይናገራል፡፡ የተላላኪነት ግባቸውን ለመምታትም ሀገር ውስጥ ያሉትን የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎችና እንደ "መድረክ" ዓይነት አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተከታይ መሳይ "ቡችላዎችን" ጩኸት በሬዲዮናቸው ያስተጋባሉ፡፡

ይህ ብቻም እንዳይመስላችሁ፡፡ ጋዜጠኞቹ ራሳቸው በጥላቻ ፖለቲካ የሚመሩና ሁልጊዜም ሁኔታዎችን ከሀገራችን ውድቀትና አለመረጋጋት አንፃር የሚያዩ ናቸው፡፡ እንዲያውም ከዘገባዎቻቸው በኋላ "እያንዳንዱን አሉታዊ ተግባር በመደገፍ ምን ያህል የኢትዮጵያን ልማት አደናቅፈናል?" የሚል የሂስና ግለሂስ ግምገማ የሚቀመጡ ይመስለኛል፡፡ እስቲ ለማንኛውም ይህን አባባሌን በአንድ ወቅት ከተከሰተ የቪ.ኦ.ኤ. ዘገባ ጋር በማስተሳሰር ለውድ አንባቢዎቼ እንካችሁ ልበል።…

…ጊዜው ትንሽ ቆየት ይላል። ምናልባትም አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ሳይሆነው የሚቀር አይመስለኝም። በወቅቱ ትግራይ ክልል ውስጥ “እንደርታ” የሚባል አካባቢ በህገ - ወጥ መንገድ ቤት የገነቡ ግለሰቦችን የተመለከተ ዘገባ ግርማይ ገብሩ የተባለ የቪ.ኦ.ኤ. የመቀሌ ሪፖርተር ያቀርባል፡፡

ታዲያ ዘጋቢው የጋዜጠኝነት ሙያዊ አሰራር በሚፈቅደው መሰረት፤ ቤታቸው የፈረሰባቸውን ግለሰቦችና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የተለያዩ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችን ያነጋግራል፡፡ በዚህም ሚዛናዊ የሆነ ዘገባን ያቀርባል፡፡ ይሁንና አንድ አስገራሚ ክስተት በመሃከሉ ተፈጠረ። ይኸውም ሪፖርቱ በተላለፈ ማግስት ባሉት ቀናት ውስጥ የዘጋቢው ስም የቪ.ኦ.ኤ. የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ እርፍ ማለቱ ነው፡፡

እርግጥ በዚያን ምሽት በፅንፈኞቹ ተላላኪዎች ጓዳ ውስጥ መተረማመስ ሳይፈጠር የቀረ አይመስለኝም፡፡ ለወትሮው ቢሆን የዋሽንግተኖቹ ፖለቲከኛ ጋዜጠኞች እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ሲያገኙ ቤት የፈረሰባቸውን ግለሰቦች ብቻ በማነፍነፍ ያራግቡና ወደ ኢትዮጵያ ስልክ ሳይደውሉ “በጉዳዩ ላይ እገሌ ወደሚባል መስሪያ ቤት ደውለን ሊሣካልን አልቻለም፤ በሌላ ጊዜ እናቀርባለን” ብለው ካደናገሩ በኋላ፤ የውሃ ሽታ ሆነው ይቀሩ ነበር፡፡

በዚህም የኢትዮጵያ መንግስት የዜጐችን መብት የማያስከብር አስመስለው በማቅረብ የፖለቲካ ፍላጐታቸውን ያራግፉና የውሸት ዘገባ ይሰሩበታል፡፡ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ይህ የቅጥፈት ዘገባ ለአክራሪ ኒዩ-ሊበራሎቹ ለእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ አምኒስቲ ኢንተርናሽናል፣ ወዘተ ይተላለፍና መግለጫ ይሰራበታል።

እንግዲህ የመቀሌው ዘጋቢ በአራዶች ቋንቋ “የፎረሸው” እና መነጋገሪያ የሆነው ይህንኑ ባለማሣካቱ ነው፡፡ እናም በየጊዜው ስለ ጋዜጠኝነት አሰራር የሚቦተልከው ቪ.ኦ.ኤ. ተግባሩ እውነት መስሎት ሚዛናዊ ዘገባ ያቀረበው የመቀሌው ሪፖርተር፤ “ተሸውዷል” ማለት ይቻላል፡፡

በመሆኑም በተለመደውና የትኛው የቪ.ኦ.ኤ. ተላላኪ ጋዜጠኛ እንደሚፅፈው በይፋ በማይታወቀው ከአድማጮቻችን የደረሱን አስተያየቶች በሚል ሽፋን፤ ሪፖርተር

ግርማይና “ሚዛናዊ ዘገባው” የተለያዩ ስሞች እየተሰጧቸው የመቀጣጫ ያህል የውርጅብኝ ናዳ ወረደባቸው፡፡

“አስተያየት ሰጡ” የተባሉት ግለሰቦች ከቪ.ኦ.ኤ. ጣቢያ ‘ስለምን የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት እውነቱን ይናገራሉ?’ የሚል አንድምታ ያለው አስገራሚና የተቀነባበረ ፀረ- ኢትዮጵያ መልዕክት በየዕለቱ እያስተላለፉ እንዲያመሹ ተደርጓል፡፡ በወቅቱ የውርጅብኙን ናዳ ዘጋቢው እንዴት እንደ ተቋቋመው ባላውቅም፤ ምናልባት ግን ከእነማን ጋር እየሰራ እንደሆነ ከህሊናው ጋር ሙግት መግጠሙ የሚቀር አይመስለኝም፡፡

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት፤ ይህን መሰሉ የቪ.ኦ.ኤ. ጋዜጠኞች ድርጊት ሁለት ነገሮችን የሚያመላክት ነው፡፡ አንደኛው በሬድዮ ጣቢያው የሚተላለፉ ዘገባዎች በፅንፈኞቹ አለቆቻቸውና በጋዜጠኞቹ የጥላቻ ፖለቲካ ፍላጐት የሚቀርቡ እንጂ፤ ምንም ዓይነት ሙያዊ አሰራር የሌላቸው፣ ቢኖራቸውም ለይስሙላ የሚባሉ መሆናቸው ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ “የአበራሽን ጠባሣ ያየ በእሳት አይጫወትም” እንዲሉ፤ በሀገራችን የሚገኙትን የጣቢያውን ዘጋቢዎች “ሚዘናዊነት ከሚባል የተሣሣተ አስተሣሰብ ታቀቡ!” የሚል አንድምታ ያለው የማስጠንቀቂያ ደወል መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ይህን መሰሉ እኩይ ሴራቸው ዛሬ ላይ ደግሞ ወደ “ፖለቲካዊ ሃይማኖት” ደጋፊነት ተሻግሮ ሀገራችንን መረጋጋት የማይታትባት ለማስመሰልም የማይቆፍሩት የማሳሳቻ ድንጋይ የለም። እርግጥ ከሚንቀሳቀሱበት ዓላማ አኳያ ለእነ ቪኦኤ ማንኛውም መጥፎ ምግባር ተገቢና ትክክል ነው።

ትናንት በየመስጊዱ በጥቂት አክራሪዎችና የሽብር ተጠርጣሪዎች ከስነ-ምግባር ባፈነገጠ መልኩ “ኢቲቪ ምንትስ” በማለት ሲሳደቡ እንደዘገቡት ሁሉ፤ ዛሬም ጉዳዩ ከሃይማኖትነት አልፎ በግላጭ ፖለቲካዊ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ገዥውን ፓርቲ ሲወርፉት ተንሰፍስፈው እያራገቡት ነው።

ምንም እንኳን የአክራሪዎቹ ድርጊት ከኢቲቪ ስድብ ወደ ፖለቲካ ፓርቲ ስድብ መሸጋገሩ ጉዳዩ ሃይማኖታዊ ሳይሆን በግላጭ ፖለቲካዊ መሆኑን በማያሻማ መልኩ የሚያረጋግጥ ቢሆንም፣ ለእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች "ሎሌዎች" ግን ግዳይ የመጣል ያህል ይቆጠራል።

"የሰዎቹ እንቅስቃሴ ሃይማኖታዊ ነው" እያሉ የሚሞግቱ ሰዎችን ከያሉበት በባትሪ ፈልገው በማምጣት ዕውነታውን እያዛቡ ለእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች አስረጅ አድርገው ያቀርባሉ።...አባቴ ይሙት ድንቅ ጋዜጠኝነት ነው። ቂ.ቂ.ቂ....

ለጥቀውም ሁኔታውን እንደ እግር ኳስ የአጭር ቅብብል ጨዋታ እጅግ ፍጥነት በተሞላበት ሁኔታ የመቀባበል ድራማን እየከወኑ ጉዳዩን እውነት ለማስመሰል ይጥራሉ።

ማታ አንድ ሰዓት ላይ የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ ያቀረበውን ዘገባ፣ የአሜሪካው አቻው ትንሽ ጥገናዊ ለውጥ አድርጎበትና ጉዳዩን በአሉባልታ ወሬዎች አጭቆ ሀገር የፈረሰ ያህል "ዋይ...ዋይ" ያስብለዋል። እናም በየምሽቱ በቅብብሎሽ ሀገርን የማጥላላት ድራማው ትዕይንት ባህር ማዶ ቁጭ ተብሎ በዚህ መልኩ ገቢራዊ ይሆናል—ሳያሰልስ በትናንት፣በዛሬና በነገ ድቅድቅ ጨለማ ምሽቶች።

ግና ሌሊቱ ተገባዶ፣ ጨለማው በብርሃን ሲተካ ከአሉባልታ የፀዳው እውነተኛው የኢትዮጵያ ሰማይ እንደ ሁልጊዜው ጥርት ባለ ድባብ ይተካል። ከዚህ ሰማይ ስር ያሉት ታታሪዎቹ የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ስለ ትናንት ምሽቱ የቅብብሎሽ ውኸንብር አያስቡም።

የድቅድቅ ጨለማውን የተነቃበት እሳቤን ቢሰሙትም ሊያስታውሱት አይፈልጉም። እናም በልማታዊው መንግስታቸው በተመቻቸላቸው ሰፊ የዕድገት ጎዳና ያለ አንዳች እረፍት ይተማሉ።

በዚህ ጎዳና ላይም ትርፍና ኪሳራቸውን የሚያሰሉት ከተጨባጭ ተጠቃሚነታቸው አኳያ እንጂ ከበሬ ወለደ አሉባልታ ባለመሆኑ፣ "ከመዝሙሩ" ባሻገር ያሉትን የዕውነታ ፈርጦችን ፈልቅቀው በማውጣት በሃይማኖት ስም ህዝብን ለማሸበር የሚሞክሩ ጥቂት

አክራሪዎችን ከመካከላቸው እየነቀሱ ለህግ ያቀርባሉ። ፍንትው ብሎ በወጣው ኢትዮጵያዊ ብርሃን እየታገዙ የነገ "ሰውነታቸውን" ማረጋገጣቸውም አይታበይም።

እናም ባህር ማዶ ቁጭ ብለው በስሚ ስሚ አሉባልታንና ሟርትን በጭፍን ጥላቻ እየፈለሰሙ አሸባሪነትን ባልተጨበጠ ዕውነታ ላይ ተመርኩዘው "ስፖንሰር" እያደረጉ ያሉት እነ ቪ.ኦ.ኤና አምሳያዎቹ፤ ሀገር ውስጥ ያለው ዕውነታ ይህ በመሆኑ ከቻሉ ከጭፍን አታሞ ደላቂነታቸው ቢላቀቁ እሰየው ነው ባይ ነኝ።

ሆኖም በእኔ እምነት ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ዋነኛ ስራቸው በጋዜጠኝነት ሽፋን የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ተላላኪና ቃል አቀባይ ሆነው የሚሰሩ በመሆናቸው ይህን በራሳቸው ሀገር ላይ የሚፈፅሙትን "ባንዳዊ" ተግባር የሚተውት አይመስለኝም– ስራቸው "የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል" እንዲሉት ነውና።

ግና ያም ሆነ ይህ እነርሱ በሽብር ጋሻ ጃግሬነት ጨለማ ውስጥ ሆነው ሃይማኖተኛ ያልሆኑ አክራሪዎችን በመደገፍ ያሻቸውን ቢለፍፉና ቢያስለፍፉም አካሄዳቸው በምንም መልኩ የሚሰምርላቸው አይመስለኝም።

ምክንያቱም የሀገራችን ህዝብ እያንዳንዱን እንቅስቃሴውን እየተመነና ተጠቃሚነቱን በየደረጃው እያረጋገጠ የሚራመደው የብርሃን ፀዳልን ባጎናፀፈው ልማታዊውና ዴሞክራሲያዊ መንግስቱ በሳል አመራር ሰጪነት ስለሆነ ነው። የእነሱን የማደናቆሪያ "መዝሙር" የሚሰማበት ጊዜ የለውም።

እናም 'የግድ እኛን ተከተሉ' እያሉ የየሀገራቱን አንጡራ ሃብት ለመዝረፍ ባሰፈሰፉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎችና አጨብጫቢዎቻቸው አማካኝነት ህዝቡ የማይሰማውን አሰልቺ "መዝሙር" በነጭ ለባሽነት ማቀንቀን ትርፉ ትዝብት ብቻ አይመስለኝም። ከዚያም ባለፈ ተሰሚነትንና ተዓማኒነትን ገደል ትቶ መሳቂያና መሳለቂያ የሚያደርግ ይመስለኛል።